

## የማቴዎስ ፩ ሴቶች

# ረዓብ

የጥናት መምሪያ

Selah
PAUSE • REFLECT

# መግቢያ

በማቴዎስ ፩ ውስጥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ ውስጥ የአምስት ሴቶችን ስም እናያለን። ለብዙዎቻችን የዘር ሐረግ መቁጠር ከመጽሐፍ ቅዱስ ንባባችን አብልጠን የምንወደው አካል ላይሆን ይችላል። አንዳንዶቻችን ከነጭራሹ ልንዘለው እንችላለን። ሆኖም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተዘረዘሩት በእያንዳንዱ የዘር ሐረጎች ውስጥ ትኩረትን የሚስቡ አስደናቂ ነገሮችን እናያለን፣ ማቴዎስ ፩ም እንዲሁ ነው።

የሴቶች ወይም የእናቶች ስም በአይሁድ የዘር ሐረግ ውስጥ በተለምዶ አይጠቀሱም። በእውነቱ በአይሁድ ታሪክ ዝና የነበራቸውን ትውልዶች ብቻ በመጥቀስ፣ ሌሎችን በመዝለል የዘር ሐረጎችን በአጭሩ የሚጽፉ ሰዎች ስለነበሩ፣ በዘር ሐረግ ውስጥ መጠቀስ ራሱ በጣም ትልቅ ክብር ነበር። ይህንን ስናስብ እነዚህ አምስት ሴቶች ማለትም ትዕማር፣ ረዓብ፣ ሩት፣ ቤርሳቤህ እና የኢየሱስ እናት ማርያምን ማቴዎስ መጥቀሱ በእርግጥ ሊያስደንቀን ይጀምራል።

እነዚህ አምስት ሴቶች ሕይወታቸው ሲጠና ስለ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስለ ወንጌል፣ እና ስለ እለት ተእለት ሕይወት የሚነግረን ነገር አለ።

© 2020 by Selah Ministries

Published by Selah Ministries
P.O. Box 479, Addis Ababa, Ethiopia

Published in Addis Ababa, Ethiopia
All rights reserved. No part of this publication may be reproduced in any form without permission from the publisher, except in the case of brief quotations embodied in other works or reviews.

All Scripture quotations are from the NASV Amharic Bible (Holy Bible, New Amharic Standard Version (Addisu Medebegna Tirgum)) Copyright © 2001 by Biblica, Inc.®
All rights reserved worldwide.

Illustrations
Front cover: Yikunoamlak Ayalew
Back cover: Ammanuel Anbessie

# ስለ ጥናት መምሪያው

የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት ስንፈልግ መንፈስ ቅዱስ ዋና አስተማሪያችን መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ኢየሱስ “መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፤ እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያሳስባችኋል” ይለናል (ዮሐንስ 14፥26)። በጥናታችን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንዲያስተምረን፣ እንዲለውጠን ከመጠየቅ ባሻገር የሚከተሉትን ይዘው መዘጋጀት ጠቃሚ  ነው ብለን እናስባለን።

- መጽሐፍ ቅዱስ
- ማስታወሻ ደብተር (ሐሳብዎን ለማስፈሪያ ቦታ ስላለው ይህንን መምሪያ አትመው በማውጣት መጠቀም ይችላሉ)
- በመጽሐፍ ቅዱስዎ ወይም በማስታወሻዎ ውስጥ ለመጻፍ ቀለም ያላቸው እስኪብርቶዎች ወይም እርሳሶች

---

በዚህ ጥናት ውስጥ ሁሉ ራስዎን እነዚህን ጥያቄዎች እየጠየቁ ይሂዱ፥

- ይህ ክፍል ስለ እግዚአብሔር ልብ፣ መንገዶች፣ እና ባሕርይ ምን ይነግረኛል?
- ይህ ክፍል ወደ ኢየሱስ እና ወደ ወንጌል እንዴት ይጠቁማል?
- ልከተለው ወይም ላስወግደው የሚገባ ምሳሌ አለ? ከሆነስ፣ ምን ዓይነት ለውጥ ወይም ምላሽ መስጠት አለብኝ?

ተጓዳኙን የጥናት ቪዲዮ መመልከት ጠቃሚ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ። ቪዲዮውን ከዚህ በታች ያለውን ምስል በመንካት ወይም በድህረ-ገፃችን www.selahethiopia.org/rahab ያገኙታል።



# ኢያሱ 2

ከዚያም የነዌ ልጅ ኢያሱ፣ “ሄዳችሁ ምድሪቱን፣ በተለይም የኢያሪኮን ከተማ ሰልሉ” ብሎ ከሰጢም ሁለት ሰላዮች በስውር ላከ፤ ሰዎቹም ሄደው ረዓብ ከተባለች ጋለ ሞታ ቤት ገቡ፤ በዚያም ዐደሩ።

ለኢያሪኮም ንጉሥ፣ “እነሆ፤ ምድሪቱን ሊሰልሉ ጥቂት እስራኤላውያን በሌሊት ወደዚህ መጥተዋል” ተብሎ ተነገረው። የኢያሪኮም ንጉሥ፣ “ወደ አንቺ መጥተው ወደ ቤትሽ የገቡት ሰዎች ምድሪቱን በሙሉ ለመሰለል ስለ ሆነ፣ እንድታስወጪአቸው” የሚል መልእክት ወደ ረዓብ ላከ።

ሴቲቱ ግን ሁለቱን ሰዎች ተቀብላ ሸሽጋቸው ስለ ነበር፣ እንዲህ አለች፤ “በእርግጥ ሰዎቹ ወደ እኔ መጥተዋል፤ ነገር ግን ከወዴት እንደ መጡ አላውቅም። ጨልሞ የቅጥሩ በር ከመዘጋቱ በፊት ወጥተው ሄደዋል፤ በየት በኩል እንደሄዱ ግን እኔ አላውቅም፤ ልትደርሱባቸው ትችላላችሁና ፈጥናችሁ ተከታተሏቸው።” ነገር ግን ሰዎቹን ጣራ ላይ አውጥታ በረበረበችው የተልባ እግር ውስጥ ደብቃቸው ነበር። ሰዎቹም ሰላዮቹን በመከታተል ወደ ዮርዳኖስ መሻገሪያ የሚወስደውን መንገድ ይዘው ሄዱ፣ አሳዳጆቹ ወጥተው እንደሄዱም የቅጥሩ በር ተዘጋ።

ሰላዮቹ ከመተኛታቸው በፊት ሴቲቱ ወደ ጣራው ወጥታ፣ እንዲህ አለቻቸው፤ “እግዚአብሔር ይህችን ምድር እንደሰጣችሁ፣ እናንተንም መፍራት እንዳደረብን፣ የዚህች አገር ነዋሪዎች ሁሉ ልባቸው በፊታችሁ መቅለጡንም ዐውቃለሁ። ከግብፅ በወጣችሁ ጊዜ እግዚአብሔር ቀይ ባሕርን በፊታችሁ እንዴት እንዳደረቀ፣ እናንተም ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ፈጽሞ ያጠፋችኋቸውን ሁለቱን የአሞራውያን ነገሥታት፣ ሴዎንንና ዐግን ምን እንዳደረጋችኋቸው ሰምተናል። ይህን በሰማን ጊዜ ልባችን ቀለጠ፤ እናንተን ከመፍራት የተነሣም ያልተሸበረ ሰው አልነበረም፤ እግዚአብሔር አምላካችሁ በላይም በሰማይ፣ በታችም በምድር እርሱ አምላክ ነውና። እንግዲህ እኔ በጎነትን እንዳሳየኋችሁ ሁሉ፣ እናንተም በጎነትን ለአባቴ ቤት እንድታሳዩ በእግዚአብሔር ማሉልኝ፤ መተማመኛ የሚሆን ምልክትም ስጡኝ፤ የአባቴንና የእናቴን፣ የወንድሞቼንና የእኅቶቼን እንዲሁም የእነርሱ የሆነውን ነፍስ ሁሉ እንድታተርፉልኝ፤ ከሞትም አድኑን።”

ሰዎቹም፣ “የእናንተን ሞት ለእኛ ያድርገው! እኛ የምናደርገውን ሁሉ ካልተናገራችሁ፣ እግዚአብሔር ምድሪቱን በሚሰጠን ጊዜ፣ በጎነትና ታማኝነት እናሳይሻለን” አሏት።

መኖሪያ ቤቷ የከተማውን ቅጥር ተጠግቶ የተሠራ ስለ ነበር፣ ሰዎቹን በመስኮት አሾልካ በገመድ አወረደቻቸው። እርሷም፣ “የሚከታተሏችሁ ሰዎች እንዳያገኟችሁ፣ ወደ ኰረብታዎቹ ሂዱ፤ እነርሱ እስኪመለሱም ድረስ ሦስት ቀን በዚያ ተሸሸጉ፤ ከዚያ በኋላ መንገዳችሁን ትቀጥላላችሁ” አለቻቸው።

ሰዎቹም እንዲህ አሏት፤ “ባማልሽን በዚህ መሓላ የምንያዘው፣ ወደ ምድሪቱ በገባን ጊዜ፣ ይህን ቀይ ፈትል እኛን ባወረ ድሽበት መስኮት ላይ አስረሽ ካንጠለጠልሽው፣ እንዲሁም አባትሽንና እናትሽን፣ ወንድሞችሽንና የአባትሽን ቤተ ሰዎች ሁሉ ወደ ቤትሽ ካመጣሻቸው ብቻ ነው። ማንም ከቤትሽ ወጥቶ መንገድ ላይ ቢገኝ፣ ደሙ በራሱ ላይ ነው፤ እኛ አንጠየቅበትም፤ ነገር ግን ከአንቺ ጋር እቤት ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው ከተነካ የደሙ ባለ ዕዳ እኛ እንሆናለን።

እኛ የምናደርገውን ብትናገሪ ግን፣ ካስማልሽን መሐላ ነጻ እንሆናለን።” እርሷም፣ “ይሁን፤ ባላችሁት ተስማምቻለሁ” ስትል መለሰች፤ ከዚያም ሰደደቻቸው፤ እነርሱም ሄዱ፤ ቀይ ፈትሉንም በመስኮቷ ላይ አንጠለጠለችው።

እነርሱም ወጥተው ወደ ኰረብቶቹ ሄዱ፤ የሚከታተሏቸውም ሰዎች በየመንገዱ ሁሉ ላይ ፈልገውና አጥተው እስኪመለሱ ድረስ፣ ሦስት ቀን በዚያው ተሸሸጉ። ሁለቱም ሰላዮች ተመለሱ፤ ከኰረብቶቹም ወርደው ወንዞን በመሻገር፣ ወደ ነዌ ልጅ ወደ ኢያሱ መጥተው ያጋጠማቸውን ነገር ሁሉ ነገሩት። ለኢያሱም፣ “በእርግጥ እግዚአብሔር ምድሪቱን በሙሉ በእጃችን አሳልፎ ሰጥቶናል፤ በዚያ የሚኖረውም ሕዝብ ሁሉ እኛን ከመፍራቱ የተነሣ ልቡ መቅለጡን አይተናል” አሉት።

# ኢያሱ 6

በዚህ ጊዜ እስራኤላውያንን ከመፍራት የተነሣ፣ ኢያሪኮ ፈጽማ ተዘግታ ነበር፤ ወደ ውጭ የሚወጣም ሆነ ወደ ውስጥ የሚገባ አልነበረም።

እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ አለው፤ “እነሆ፤ ኢያሪኮን ከንጉሥዋና ከተዋጊዎቿ ጋር አሳልፌ በእጅህ ሰጥቻለሁ። ከተማዪቱን ከተዋጊዎቻችሁ ጋር አንድ ጊዜ ዙሩ፤ ይህንም ስድስት ቀን አድርጉ። ሰባት ካህናት፣ ሰባት ቀንደ መለከት ተሸክመው በታቦቱ ፊት ይውጡ፤ በሰባተኛውም ቀን ካህናቱ መለከት እየነፉ ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ይዙሩ። የማያቋርጥ የመለከት ድምፅ ሲነፋ በምትሰሙበት ጊዜ፣ ሕዝቡ ሁሉ ከፍ ያለ ጩኸት ያሰማ፤ ከዚያም የከተማዪቱ ቅጥር ይፈርሳል፤ ሕዝቡም ወደ ላይ ይወጣል፤ እያንዳንዱም ሰው በቀጥታ ይገባል።”

ስለዚህ የነዌ ልጅ ኢያሱ ካህናቱን ጠርቶ፣ “የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸከሙ፤ ሰባት ካህናትም ሰባት ቀንደ መለከት ይዘው በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ይሂዱ” አላቸው። ሕዝቡንም፣ “ወደ ፊት ሂዱ፤ ከተማዋን ዙሩ፤ የታጠቁ ተዋጊዎችም በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ቀድመው ይሂዱ፤ ከተማዪቱንም ዙሩ” ሲል አዘዛቸው።

ኢያሱም ለሕዝቡ ከተናገረ በኋላ፣ ሰባቱ ካህናት በእግዚአብሔር ፊት ሰባት ቀንደ መለከት ይዘው መለከታቸውን እየነፉ ወደ ፊት ቀደሙ፤ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦትም ተከተላቸው። የታጠቁ ተዋጊዎችም መለከት ከሚነፉት ካህናት ፊት ቀድመው ሲሄዱ፣ ደጀን የሆኑት ጠባቂዎች ደግሞ ታቦቱን ተከተሉ፤ በዚህ ጊዜ ሁሉ መለከቶቹ ባለማቋረጥ ይነፉ ነበር። ኢያሱ ሕዝቡን፣ “የማሸበሪያ ጩኸት አታሰሙ፤ ድምፃችሁ ከፍ ብሎ አይሰማ፤ ጩኹ እስከምላችሁም ቀን ድረስ ከአፋችሁ አንዲት ቃል አትውጣ፤ የምትጮኹት ከዚያ በኋላ ነው” ሲል አዘዛቸው።

ስለዚህ ኢያሱ የእግዚአብሔርን ታቦት ተሸክመው፣ ከተማዪቱን አንድ ጊዜ እንዲዞሩ አደረገ። ከዚያም ሕዝቡ ወደ ሰፈር ተመልሰው ዐደሩ።

ኢያሱ በማግሥቱ ማልዶ ተነሣ፤ ካህናቱም የእግዚአብሔርን ታቦት ተሸከሙ። ሰባቱም ካህናት ሰባት ቀንደ መለከት ይዘው በእግዚአብሔር ታቦት ፊት እየሄዱ፣ መለከቱን ባለማቋረጥ ይነፉ ጀመር፤ የታጠቁ ተዋጊዎችም እነዚህን በመቅደም

ሲሄዱ፣ የደጀን ጠባቂዎቹ ደግሞ የእግዚአብሔርን ታቦት ይከተሉ ነበር፤ ካህናቱም ሳያቋርጡ መለከት ይነፉ ነበር። በሁለተኛውም ቀን ከተማዪቱን አንድ ጊዜ ከዞሩ በኋላ ወደ ሰፈር ተመለሱ፤ ስድስት ቀን ሙሉም እንዲሁ አደረጉ።

በሰባተኛው ቀን ገና ጎሕ ሲቀድ ተነሡ፤ እንደ በፊቱም ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ዞሩ፤ ከተማዪቱን ሰባት ጊዜ የዞሯትም በዚያን ቀን ብቻ ነው። በሰባተኛው ዙር ላይ ካህናቱ መለከቱን ሲነፉ፣ ኢያሱ ሕዝቡን እንዲህ ሲል አዘዘ፤ " እግዚአብሔር ይህችን ከተማ ሰጥቶአችኋልና ጩኹ ከተማዪቱና በውስጧ ያለው ሁሉ ለእግዚአብሔር የተለየ ስለ ሆነ ፈጽማችሁ አጥፉ ፣ እኛ የላክናቸውን ሰላዮች ስለሸሸገች ጋለሞታዪቱ ረዓብ ብቻና ከእርሷ ጋር በቤቷ ውስጥ ያሉት ሁሉ ይትረፉ።

እናንተ ግን እርሞ ከሆኑት ነገሮች አንዳች በመውሰድ በራሳችሁ ላይ ጥፋት እንዳታመጡ እጃችሁን ሰብስቡ፤ ያለዚያ የእስራኤልን ሰፈር ለጥፋት ትዳርጋላችሁ፤ ክፉ ነገር እንዲደርስበትም ታደርጋላችሁ፤ ብሩና ወርቁ እንዲሁም የናሱና የብረቱ ዕቃ ሁሉ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ስለ ሆነ፣ ወደ እግዚአብሔር ግምጃ ቤት ይግባ።"

መለከቱ ሲነፋ ሕዝቡ ጮኸ፤ የመለከቱ ድምፅ ተሰምቶ፣ ሕዝቡ በኀይል ሲጮኽ ቅጥሩ ፈረሰ፤ እያንዳንዱ ሰው ሰተት ብሎ ገባ፤ ከተማዪቱም በእጃቸው ወደቀች። በከተማዪቱ ውስጥ ያለውን ሁሉ ማለትም ወንዱንና ሴቱን፣ ወጣቱንና ሽማግሌውን፣ ከብቱንና በጉን እንዲሁም አህያውን በሰይፍ ስለት ፈጽመው አጠፉ።

ኢያሱ ምድሪቱን የሰለሉትን ሁለቱን ሰዎች፣ "ወደ ጋለሞታዪቱ ቤት ሂዱ፤ በማላችሁላትም መሠረት እርስዋንና የእርሷ የሆነውን ሁሉ ከዚያ አውጡ" አላቸው። ስለዚህ ሁለቱ ወጣት ሰላዮች ገብተው ረዓብን፣ አባቷንና እናቷን፣ ወንድሞቿንና የእርሷ የሆኑትን ሁሉ ከዚያ አወጧቸው። ቤተ ዘመዶቿንም ሁሉ አውጥተው ከእስራኤል ሰፈር ውጭ አስቀመጧቸው።

ከዚያም ከተማዪቱን በሙሉ፣ በውስጧ ያለውንም ሁሉ አቃጠሉ፤ ብሩንና ወርቁን፣ የናሱንና የብረቱን ዕቃ ግን በእግዚአብሔር ግምጃ ቤት አኖሩ። ኢያሪኮን እንዲሰልሉ ኢያሱ የላካቸውን ሰዎች ስለ ደበቀች፣ ጋለሞታዪቱን ረዓብን፣ ቤተ ሰቧንና የእርሷ

የሆኑትን ሁሉ አደናቸው፤ እርሷም እስከ ዛሬ ድረስ በእስራኤላውያን መካከል ትኖራለች።

በዚያን ጊዜም ኢያሱ፣ እንዲህ ሲል ማለ፤ “ይህችን ከተማ መልሶ የሚሠራት ሰው በእግዚአብሔር ፊት የተረገመ ይሁን፤

“መሠረቷን ሲጥል፣
  የበኵር ልጁ ይጥፋ፤
ቅጥሮቿንም ሲያቆም፣
  የመጨረሻ ልጁ ይጥፋ” ብሎ ማለ።

ስለዚህ እግዚአብሔር ከኢያሱ ጋር ነበር፤ ዝናውም በምድሪቱ ሁሉ ላይ ወጣ።

# ረዓብ

**ኢያሱ 1-6 | ማቴዎስ 1፥5 | ዘዳግም 18፥9-14 እና 20፥17-18 | ዘኍልቍ 33፥50-53**

የረዓብን ማንነት፣ ህይወት እንዲሁም በወንጌል ውስጥ ስላላት ሚና በጥልቀት ለማጥናት ከዚህ በላይ ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያንብቡ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልከቱ፤ ያሰላስሉ።

**ኢያሱ 2፥1-14**

- የኢያሪኮ ህዝብ ለምን የእግዚአብሔር ህዝብ ጠላት ሆነ?

- ሰላዮቹ በኢያሪኮ ሲደርሱ የረዓብን ቤት ለምን የመረጡ ይመስላችኋል?

- ረዓብ ሰላዮቹን ለመጠበቅ ምን አደረገች?

- በምላሹ ምን ትጠይቃለች?

- ረዓብ ስለ እስራኤላውያን አምላክ ምን ሰምታለች? በዝርዝር እናስብ

- ከሰላዮቹ ጋር በነበራት ንግግር እና ግንኙነት ስለ ረዓብ እምነት ምን ማለት እንችላለን? (መዝሙር 111፥10)

- ረዓብ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔርን የፈራችበት መንገድ በኢያሪኮ ካሉ ሌሎች ሰዎች ፍርሐት በምን ይለያል?

**ኢያሱ 2፥5-24**

- የቀይ ፈትሉ ዓላማ ምን ነበር?

- ቀዩ ፈትል የምን ምልክት ነው? ረዓብን እና ቤተሰቧን ማዳን የቻለው ለምንድነው? (ዘጸአት 12፥13-28 እና ራእይ 5፥9)

- የኢያሪኮ ዕጣ ፈንታ ምን ነበር? ሁሉም ነገር ለምን ተደመሰሰ?

**ኢያሱ 6**

- የረዓብ እምነት በምን መልኩ እንዴት ተሸለመ?

- የያዕቆብ መጽሐፍ (2፥20-24) ረዓብን እንደ ዋና የእምነት ምሳሌ ይጠቅሳታል። ያዕቆብ እንዲሁ ከሥራ ውጭ ያለ እምነት የሞተ መሆኑን በቁጥር 26 ላይ ይገልፃል። እምነት እና ሥራ በረዓብ ታሪክ ውስጥ እንዴት አብረው ይሠራሉ?

- በአዲስ ኪዳን ውስጥ ረዓብ እንዴት ትታወሳለች? (ዕብራውያን 11፥31 እና ያዕቆብ 2፥25-26)

# የአሰላስሎት ጥያቄዎች

የረዓብ አዳዳን ተሞክሮ ከእኛ አዳዳን ጋር እንዴት ይመሳሰላል? ከምንስ አዳነን? እናም የእግዚአብሔር መሆናችንን የሚያሳየን ምንድነው?
**የጥሞና ጥቅስ ኤፌሶን 2፥11-22**

---

በረዓብ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ የደረገው ተጋድሎ የኢያርኮን ሕዝብ ልብ ሲያንበረክክ እናያለን። ይህን ስናነብ እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገውን መናገራችን ምን ያህል ትልቅ ፋይዳ ሊኖረው እንደሚችል እንረዳለን። እስቲ እግዚአብሔር በህይወቴ አደረገልኝ ብለን የምናስባቸውን፤ የሀይሉን፣ የወንጌሉን እና የምህረቱን ምስክርነቶች እናስብ፣ እንዘርዝር፣ እነዚህንስ ለማን ልናጋራቸው እንችላለን?

---

ትዕግስታችንን ወይም እምነታችንን የሚፈትኑ ነገሮች ወደ ሕይወታችን ሲመጡ እንዴት እምነታችንን ማበርታት እንችላለን? ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መንገዶች በማሰብ የራሳችንን ልምምድ እንመርምር። ከእነዚህ ውስጥ ልናደግበት የሚገባ አለ? ሞክረነው ጥሩ እመርታ ያየንበት አለ?

- የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት/በማንበብ
- የእግዚአብሔርን ማንነት በማሰላሰል
- እግዚአብሔር በህይወታችን ያደረገውን በማሰብ
- ከክርስቲያን ህብረት ጋር መቀላቀል እና ተጋላጭ መሆን

**የጥሞና ጥቅሶች (ሮሜ 10፥17 | ማቴዎስ 4፥4 | መዝሙር 9፥1 | መዝሙር 77፥11 | መዝሙር 105፥5 | መዝሙር 111፥1-2 | መዝሙር 143፥5 | ምሳሌ 27፥17 | ዕብራውያን 10፥24-25 | ገላቲያ 6፥2 | መዝሙር 133፥1)**

# አሰላስሉት



Selah
PAUSE • REFLECT

# ጥበብ

የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፤ ነፍስንም መልሶ
ያለመልማል፤ የእግዚአብሔር ሥርዐት የታመነ
ነው፤ አላዋቂውን ጥበበኛ ያደርጋል፡፡

መዝሙር 19:7

**ሁሉንም የሴላ ጥበብ ጥናቶች ለማግኘት**

www.selahethiopia.org/studies